# የኢትዮጵያ ፓርላማ

በዴሞክራሲ ስም ምርጫ ተካሂዶ
ሕዝቡ ድምፁን ቢሰጥ ነፃነቱን ወዶ
የወያኔ ጎራ ተመታ ግንባሩ
ዘረኛው አገዛዝ ተናደ ከስሩ።

ምነው አይገባቸው ሕዝቡ ሲጠላቸው
እነሆድ ዓምላኩ አንጎል የሌላቸው
ውሸትና ቅጥፈት ክህደት ቀለባቸው
የታሪክ ጉድፎች የአገር ጠላት ናቸው።

ኮሮጆ መገልበጥ በቁጥር ማጭበርበር
ተቃዋሚውን ኀይል መግደልና ማሰር
መዋሸት ማዋከብ ሕዝብን ማደናገር
የፋሽስት ሥራ ነው እውነቱ ይነገር።

ሽህ አዋጅ ቢታወጅ ወያኔ ቢያናፋ
ቁርጡ ቀን ተቃርቧል አትቁረጡ ተስፋ።

የአውሮፓው ኅብረት የታዘበውን
የወያኔን ስርቆት ያጋለጠውን
መለስ ባንደበቱ garbage ያለውን
የካርተርም ማዕከል የተሰማውን
የአሰራሩን ጉድፈት የምርጫ ቦርዱን
ሁሉም ስለሚያውቀው የሐቅን መቀበር
እሪ በል ወገኔ ሌባ ገብቷል በአገር
የኢትዮጵያ ጠላት ይገልበጥ ይመንጠር።

ይህች አገራችን የሁላችን ቤት
የሙጥኝ የያዛት ረሀብ ደህነት
በሽታ ልመና ኋላ ቀርነት
የአምባገነን ሥርዓት ሽብር ጦርነት
ከፊታችን ይጥፉ ጥርግርግ ይበሉ
የፈለገው ቢሆን የሕዝብ ነው ድሉ።

በሕገ አራዊት የሚያስተዳድሩ
ጠባብ ትምክህተኞች እስካሉ ባገሩ
በሽታም አይድንም ረሀብም አይጠፋ
የወያኔ ተንኮል ይታወቅ በይፋ።

ፍትህ እኩልነት መብትና ነፃነት
ሲጠፉ ከኢትዮጵያ ሲስፋፋ ባርነት
ሠላም ሲንኮታኮት በሽፍጥ በጦርነት
ሕዝባችን ሲታመስ እንደ ገና ቆሎ
አኩሪው ታሪካችን ሲዋረድ ተቃሎ
እንዴት ዝም ይባላል እሪ በል አበሻ
የእናትህን ገዳይ አሳጣው መድረሻ።

ሠላም የሚያመጡ ለእድገት የሚሰሩ
ነፃነትን አቅፈው መብትን የሚያስከብሩ
የኢትዮጵያ ልጆች ስላሉ ባገሩ
ተስፋችሁ ይጠንክር በርቱ ተባበሩ።

ፓርላማኮ ማለት የሕዝብ አዳራሽ ነው
ለወያኔ ብቻ ያስረከበው ማነው
በጡንቻ እገዛለሁ ከሆነ ነገሩ
ይኽ አያዋጣም ከታሪክ ይማሩ።

እንያ የአጋዚ ጦር ሰለባ የሆኑ
ሠላማዊ ዜጎች በቀን ሲረሸኑ
ጉዱ ፈልቶ ወጣ ታወቀ ሚስጥሩ
የወያኔ መልኩ ተፈጥሮው ተግባሩ።

የአራት ኪሎው ግቢ ፓርላማው ያለበት
ታንክና መትረየስ የተጠመደበት
አንድም ኢትዮጵያዊ ዝር የማይልበት
ለኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ መመለስ አለበት።

የኢትዮጵያ ፓርላማ ነፃ የወጣ ለት
የኢትዮጵያ ትንሳኤ የኢትዮጵያ ልደት።